# ከዲኑ ፡ የተሰጠ ፡ የመጀመሪያ ፡ ዓመት ፡ ሪፖርት ፡

ከጄምስ ፡ ሲ ፡ ኤን ፡ ፖውል ፡

የሕግ ፡ መምህርና ፡ የሕግ ፡ ትምርት ፡ ቤት ፡ (ፋኩልቲ) ዲን ፡

የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ።

የወደፊቱ ፡ ትውልድ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤትን ፡ የዕድገት ፡ ታሪክ ፡ ተከታትሎ ፡ ለመረዳት ፡ እንዲችል ፡ በየጊዜው ፡ በሚታተመው ፡ በያንዳንዱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ የሚወጣ ፡ ከቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የሕግ ፡ ዲን ፡ የሚዘጋጅ ፡ ሪፖርት ፡ እንዲኖር ፡ የመጽሔቱ ፡ አዘጋጅ ፡ ቦርድ ፡ ሐሳብ ፡ አቅርቧል ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ የወደፊት ፡ እቅድና ፡ ዝግጅትን ፡ ሳይሆን ፡ የተፈጸመውን ፡ ብቻ ፡ ለመግለጽ ፡ እንሞክራለን ።

እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ሲመረቅ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የሚከተለውን ፡ ተናግረው ፡ ነበር ።

“የራሳችንን ፡ ተማሪዎች ፡ በማሠልጠን ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎችን ፡ ለማግኘት ፡ እንድንችል ፡ በቅርቡ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲከፈት ፡ እናደርጋለን ። ...... በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛታችን ፡ በአስተዳደርና ፡ በንግድ ፡ ረገድ ፡ በተለይም ፡ በራሳችን ፡ ሕጎችና ፡ ልማዶች ፡ የሠለጠኑ ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎችን ፡ ይፈልጋል ።”

እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ መስከረም ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግርማዊነታቸው ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ ቻንስለር ፡ በመሆናቸው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤትን ፡ በደንብ ፡ መርቀው ፡ ከፈቱ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የፎርድ ፡ ፋውንዴሽን ፡ ከሰጠው ፡ የገንዘብ ፡ ዕርዳታ ፡ ጋር ፡ ደንበኛ ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ተጀመረ ።

## የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት

### አስፈላጊነት ፡

በዩኒቨርሲቲ ፡ ደረጃ ፡ በሕግ ፡ ትምህርት ፡ ሠልጥነው ፡ የተመረቁ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ቍጥር ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ነው ። በዚህ ፡ መሥመር ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የሰው ፡ ችሎታ ፡ መጨመር ፡ ሀገሪቷ ፡ በቅድሚያ ፡ የምትፈልገው ፡ ጉዳይ ፡ ስለሆነ ፡ በእኛ ፡ አስተያየት ፡ ከሁሉ ፡ በፊት ፡ የሚታሰብበት ፡ ተግባር ፡ ነው ።

ኢትዮጵያ ፡ ሰፊ ፡ የሚደነቅ ፡ የቆየ ፡ የሕግ ፡ ባህል ፡ ስላላት ፡ ልትኮራ ፡ እንደሚገባት ፡ የታወቀ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ አዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ዘመናዊ ፡ የሕግ ፡ አስተያየቶችን ፡ አሟልተው ፡ ያዘሉ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ በደንብ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉን ፡ የሚያረጋግጥም ፡ በሕግ ፡ ተወስኖ ፡ የመተዳደር ፡ ልምድ ፡ ተሟልቶ ፡ የተውጣጣና ፡ የተጣራ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡

ሕግ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ የባሕር ፡ ሕግ ፡ እና ፡ በመጨረሻም ፡ እነዚህን ፡ በሥራ ፡ ለማዋል ፡ የሚያስችሉና ፡ በተለይም ፡ ለሀገሪቱ ፡ የኢኮኖሚና ፡ የሶሻል ፡ ዕድገት ፡ መሠረት ፡ የሆኑ ፡ የምክር ፡ ቤት ፡ አዋጆች ፡ ተጠናቀው ፡ ስላሏት ፡ በዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ እርምጃዋም ፡ ልትኮራ ፡ ይገባታል ።

ነገር ፡ ግን ፡ በቂ ፡ የተራቀቀ ፡ ሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ የሰፈረ ፡ ቢሆንም ፡ በዚሁ ፡ መሥመር ፡ ጠልቀው ፡ የተማሩ ፡ ሰዎች ፡ በብዛት ፡ እንደሚያስፈልጉ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ሕግ ፡ ዘመናዊ ፡ ሲሆን ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ በጣም ፡ የተራቀቀ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ የሚተዳደርበት ፡ ሕዝብም ፡ አስተያየቱና ፡ ፍላጎቱ ፡ የተራቀቀ ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ ጠልቀው ፡ የሚረዱ ፡ በቂ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ የሚጠይቅ ፡ ይሆናል ። ኢትዮጵያም ፡ እነዚህ ፡ ዘመናዊ ፡ ሕጎቿ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውሉ ፡ የሚችሉት ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ በሰፊው ፡ የተመራመሩና ፡ የተማሩ ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎችን ፡ ያፈራች ፡ እንደሆን ፡ ነው ።

የፍርድ ፡ አመራር ፡ በሌላው ፡ ክፍል ፡ ባለው ፡ እርምጃ ፡ ላይ ፡ ተደግፎ ፡ ሊሄድ ፡ የሚችል ፡ ትርፍ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ደንበኛ ፡ የፍርድ ፡ አስተዳደር ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ሆስፒታል ፡ መገናኛና ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በቅድሚያ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ደንበኛ ፡ የፍርድ ፡ አመራር ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆነው ፡ በሦስት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ምክንያቶች ፡ የተነሣ ፡ ነው ። መጀመርያ ፡ ረቂቅ ፡ የሆነ ፡ የመብት ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ሁለተኛ ፡ ሕግ ፡ ከሌለ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ይፈርሳል ፡ ሦስተኛ ፡ ለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገትና ፡ መሻሻል ፡ ዋና ፡ መሣሪያ ፡ ነው ። እኔ ፡ እንደማምነው ፡ ማናቸውም ፡ ሕዝብ ፡ በፍርድ ፡ ረገድ ፡ ከሆነ ፡ ገና ፡ በማደግና ፡ በመሻሻል ፡ ላይ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ዳኝነት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለይቶ ፡ ፍችውን ፡ ለመረዳትና ፡ በትክክል ፡ ለመምራት ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ በመሆኑና ፡ ዳኝነትና ፡ ፍርድ ፡ በታማኝነት ፡ በጠቢብነትና ፡ በተመራመረ ፡ አእምሮ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ደግሞ ፡ ከእነዚህ ፡ ፍላጎቶች ፡ ውስጥ ፡ አብዛኛውን ፡ አሟልቶ ፡ ይዞ ፡ ባለመገኘቱ ፡ ነው ። ማናቸውም ፡ ሕዝብ ፡ ተሟልቶ ፡ የተሻሻለ ፡ የዳኝነት ፡ አሠራር ፡ ስለሌለው ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ሁሉም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀረ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በመጻሕፍት ፡ የሰፈሩ ፡ የሕግ ፡ ሐሳቦችና ፡ እነዚህን ፡ አጣርተው ፡ የሚመራመሩ ፡ ሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ብዛት ፡ ከሌላው ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ሲሆን ፡ ልክ ፡ ወደኋላ ፡ እንደመቅረት ፡ ያህል ፡ የሚያሳስብ ፡ ነው ።

የተለመደውን ፡ አገልግሎትና ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞችን ፡ ለማሟላት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሌላም ፡ መሥመር ፡ ቢሆን ፡ ሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ በጣም ፡ ተፈላጊ ፡ ናቸው ። እኔ ፡ እንደሚታየኝ ፡ በሌላ ፡ በማናቸውም ፡ መሥመር ፡ በኩል ፡ በተጣራ ፡ አስተያየት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ መሻሻል ፡ ለማድረግ ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ያስፈልጋሉ ። በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ፕላን ፡ ውስጥ ፡ "መሻሻል" የሚለው ፡ ቃል ፡ ከብዙው ፡ ፍችው ፡ ውስጥ ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ ሕጎችንና ፡ ሌሎች ፡ ስለ ፡ እርሻ ፡ ልማትና ፡ የመሬት ፡ ሀብቶች ፡ ለመሻሻል ፡ የሚረዱትን ፡ ሕጎችን ፡ ስለ ፡ ኢንቬስትሜንትና ፡ ስለ ፡ ባንክ ፡ ዕድገቶች ፡ ለአውራ ፡ ጐዳናዎች ፡ ለአይሮፕላን ፡ ማረፊያዎች ፡ ወይም ፡ ለማዕድን ፡ ሀብቶች ፡ ወይም ፡ ለእርሻ ፡ ልማትና ፡ ይህንን ፡ ለመሳሰሉት ፡ መሬት ፡ ለይቶ ፡ በማኖር ፡ በጥቅም ፡ ስለማዋል ፡ እንዲሁም ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ሕጎችን ፡ እና ፡ የተስፋፋና ፡ የተሻሻለ ፡ የገቢ ፡ ምንጭ ፡ የሚገኝባቸውን ፡ ሁሉ ፡ ስለማሻሻል ፡ ጨምሮ ፡ የያዘ ፡ ቃል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ልማት ፡ ማለት ፡ የተስፋፋ ፡ የኢኮኖሚ ፡ ተግባር ፡ መዘርጋት ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ባለሀብቶችና ፡ መንግሥታት ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ውሎችን ፡ ሊያስከትል ፡ ነው ። ስለ ፡ ስምምነትም ፡ የተሻሻለና ፡ የረቀቀ ፡ ዘዴ ፡ መፍጠርን ፡ ከታላላቅ ፡ ባለሀብቶች ፡ ጋር ፡ በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ መላላክንና ፡ መነጋገርን ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የኢኮኖሚ ፡ ድርጅቶች ፡ ቻርተሮችና ፡ አቋሞች ፡

በሕግ ፡ ወስኖ ፡ ማዘጋጀትን ፡ ሊጠይቅ ፡ ነው ። በዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመራመድ ፡ ከተፈለገ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሕጎችን ፡ በጥንቃቄ ፡ በማዘጋጀት ፡ አመንጭቶ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋልን ፡ በቅድሚያ ፡ የሚጠይቅ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሊገኝ ፡ የሚችለው ፡ በጣም ፡ ጠልቀው ፡ በመመራመር ፡ ያጠኑ ፡ የሕግ ፡ ችሎታ ፡ ያገኙ ፡ አገልጋዮች ፡ ሲኖሩ ፡ ነው ። ብዙ ፡ ስለ ፡ ልማት ፡ ዕድገት ፡ የተዘጋጁ ፡ ጽሑፎች ፡ በግልጽ ፡ እንደሚያስረዱት ፡ ማናቸውም ፡ የልማት ፡ ዕቅድ ፡ በደንብ ፡ ተጣርቶ ፡ የተዘጋጀ ፡ ቢሆንም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ውሎ ፡ ውጤት ሊያስገኝ ፡ የሚችለው ፡ በየመሥመሩ ፡ ተፈላጊውን ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ የተገኙ ፡ እንደሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

በመጨረሻ ፡ በሕግ ፡ በመመራት ፡ በሚፈለግበት ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ከዚህ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ አገልግሎት ፡ የሚሰጡበትም ፡ መሥመር ፡ አለ ። ይኸውም ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ያላቸው ፡ ለራሳቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለሌሎች ፡ መብትና ፡ ጥቅም ፡ የመሥራት ፡ ኀላፊነት ፡ አለባቸው ። ኢትዮጵያ ፡ ክርክርና ፡ የሐሳብ ፡ ልዩነት ፡ ሲፈጠር ፡ በሕግ ፡ ተመርኩዞ ፡ የመወሰን ፡ ባኅሏ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ የቆየ ፡ ልምድ ፡ በዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ እየተገለገለ ፡ ለሚሻሻል ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እንዲሠራ ፡ ማድረግ ፡ የሚፈለግ ፡ ዋና ፡ ግብ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

## የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሲመሠረት ፡ የሚገጥሙ ፡ ችግሮች ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ዕውቀትን ፡ ለማስፋፋት ፡ የሚረዱ ፡ ድርጅቶችን ፡ ለመመሥረት ፡ ሲፈለግ ፡ ብዙ ፡ ሊገጥሙ ፡ የሚችሉ ፡ አስደናቂ ፡ ሁኔታዎች ፡ አሉ ።

የእነዚህም ፡ ችግሮች ፡ ዋና ፡ መነሻ ፡ ምክንያቶች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ፡ በጣም ፡ የተለያዩና ፡ ብዙ ፡ በመሆናቸው ፡ የሕጎቹን ፡ መሠረት ፡ ጠንቅቆ ፡ ለመረዳት ፡ ብዙ ፡ ቋንቋዎችን ፡ ማወቅ ፡ ማስፈለጉና ፡ የዘመናዊ ፡ ሕጎችን ፡ መሠረታዊ ፡ ምንጭ ፡ በደንብ ፡ አብራርተው ፡ የሚያስረዱ ፡ ጽሑፎች ፡ አለመገኘት ፡ ናቸው ።

አብዛኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የግል ፡ መብት ፡ ነክ ፡ ሕጎች ፡ የተመሠረቱት ፡ በ"ሲቪል ፡ ሎው" አስተያየት ፡ ላይ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ በደንብ ፡ ለማስተማር ፡ የ"ኮንትኔንታል" ሕግን ፡ ጠንቅቆ ፡ ማወቅንና ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ቋንቋን ፡ ችሎታ ፡ የሚጠይቅ ፡ ነው ። ሌሎቹ ፡ ክፍሎች ፡ ማለት ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትና ፡ ጠቅላላ ፡ መብትን ፡ የሚገልጹ ፡ ሕጎች ፡ (ፐብሊክ ፡ ሎው) በ"አንግሎ –አሜሪካን" አስተያየት ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ስለሆኑ ፡ በእነዚህ ፡ በኩል ፡ ያሉትን ፡ ሕጎች ፡ በደንብ ፡ ለማስተማር ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ሕግ ፡ የሠለጠኑ ፡ አዋቂዎችን ፡ ማግኘትን ፡ ይጠይቃል ። በሌላ ፡ መሥመር ፡ ያሉት ፡ ሕጎች ፡ ደግሞ ፡ ለምሳሌ ፡ ስለ ፡ መሬትና ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ የሚገልጹት ፡ ሕጎች ፡ የቆየ ፡ የሀገር ፡ ባህልንና ፡ ስለዚሁ ፡ የሚመለከቱትን ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ሕጎችንም ፡ ማወቅን ፡ ይጠይቃሉ ። በሕግና ፡ በኢኮኖሚ ፡ ልማት ፡ መካከል ፡ ያሉትን ፡ ግንኙነቶች ፡ የሕግ ፡ ሊቆች ፡ ተመራምረው ፡ በደንብ ፡ ለመረዳት ፡ የጀመሩት ፡ በቅርቡ ፡ ስለሆነ ፡ በጣም ፡ አዲስ ፡ ከሆነ ፡ የዕውቀት ፡ ምርምር ፡ ላይ ፡ የሚጥለን ፡ ጉዳይ ፡ ነው ።

አማርኛ ፡ ኦፊሲዩል ፡ ቋንቋ ፡ በመሆኑ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ፡ የሕግ ፡ ጥናቶች ፡ እና ፡ ሌሎች ፡ ማናቸውም ፡ ሕግ ፡ ነክ ፡ ተግባሮች ፡ የሚገኙትም ፡ ሊጠኑ ፡ የሚገባቸውም ፡ በዚሁ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ። ባንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ሕጎቹ ፡ ሲጠኑ ፡ የተረቀቁት ፡ በፈረንሳይኛ ፡ በመሆኑ ፡ የሕጎችን ፡ መሠረተ– ሐሳቦች ፡ ለማግኘት ፡ የሚቻለው ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ቋንቋ ፡ እርዳታ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ እንግሊዝኛ ፡ ደግሞ ፡ ከፍ

ተኛ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጥበት ፡ ቋንቋ ፡ በመሆኑ ፡ የሕግ ፡ ሐሳቦችና ፡ ምርምር ፡ የሚደረግበት ፡ ቋንቋ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ይህም ፡ ማለት ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ለማሰብና ፡ ለመመራመር ፡ እንዲችሉ ፡ መርዳት ፡ ሲኖርብን ፡ በንባብና ፡ በጥናት ፡ የሕጎችን ፡ መሠረተ-ሐሳብ ፡ እንዲረዱ ፡ ፈረንሳይኛ ፡ በግዴታ ፡ ተጨማሪ ፡ መሣርያ ፡ ስለሆነ ፡ ፈረንሳይኛ ፡ ማንበብና ፡ መረዳት ፡ እንዲችሉ ፡ ማድረግ ፡ ይኖርብናል ፡ ማለት ፡ ነው ። በተጨማሪ ፡ በሁለቱ ፡ ቋንቋዎች ፡ በመሠራቱ ፡ በግዴታ ፡ ሊኖሩ ፡ የሚችሉትንና ፡ በትርጉም ፡ አለመሟላት ፡ የሚፈጠሩትን ፡ የሕግ ፡ ሐሳብ ፡ ልዩነቶች ፡ እንዴት ፡ ለማስታረቅ ፡ እንደሚቻል ፡ ማወቅና ፡ ዘዴውን ፡ ማመንጨት ፡ ሌላው ፡ ተጨማሪ ፡ ተግባር ፡ ሊሆን ፡ ነው ።

በመጨረሻም ፡ ሊገለጽ ፡ የሚገባው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ፡ ሲዘጋጅ ፡ የተደረገው ፡ የሐሳብ ፡ ክርክርና ፡ ውሳኔ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ፡ ሪፖርቶች ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሕጎች፡ ምንጭ ፡ የሚገልጽ ፡ መጽሐፍ ፡ አለመኖሩን ፡ ነው ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የእኛ ፡ ሁኔታ ፡ ከብዙ ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ሕጎችን ፡ እንዳለ ፡ ሳይለወጡ ፡ ከወረሱት ፡ የአፍሪካ ፡ ሀገሮች ፡ የተለየ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ መምህራኖቻችን ፡ በግዴታ ፡ የማስተማሪያ ፡ መጻሕፍትና ፡ ሕጎች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዴት ፡ ተተርጉመው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንደዋሉ ፡ የሚገልጹ ፡ የውሳኔ ፡ መጽሔቶችን ፡ ራሳቸው ፡ ማዘጋጀት ፡ ሊኖርባቸው ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ተግባር ፡ በጣም ፡ የሚያከብደው ፡ ለጊዜው ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ አንቀጾች ፡ የምክር ፡ ቤት ፡ ክርክርን ፡ የሚገልጹ ፡ ታሪካዊ ፡ ሬኮርዶች ፡ አለመኖራቸው ፡ እንዲሁም ፡ በጽሑፍ ፡ ተጠናቀው ፡ የሚገኙት ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ፡ በጣም ፡ ያነሱ ፡ በመሆናቸውና ፡ በሌላ ፡ በኩልም ፡ የሚረዱ ፡ በቂ ፡ ጽሑፎች ፡ ባለመኖራቸው ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ ሁኔታዎች ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መምህራን ፡ በመምረጥ ፡ ለጥናት ፡ ሊሰጠው ፡ የሚገባውን ፡ ቀደምትነት ፡ በመወሰንና ፡ በጠቅላላው ፡ የትምህርት ፡ እርምጃ ፡ ፕላን ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ ለማናቸውም ፡ አስተያየት ፡ መነሻ ፡ በመሆን ፡ የተግባራችንን ፡ አካሄድ ፡ የሚወስኑ ፡ ናቸው ። እነዚህን ፡ ችግሮች ፡ ለመከላከል ፡ እንዲቻል ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መምህራን ፡ እስካልተገኙ ፡ ድረስ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ የሠለጠኑ ፡ ከተለያየ ፡ ምንጭ ፡ የመጡ ፡ መምህራንን ፡ መቅጠር ፡ ሊያስፈልግ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ ደግሞ ፡ በተለይም ፡ አንድ ፡ ድርጅት ፡ ገና ፡ በማደግ ፡ ላይ ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡ ሊኖር ፡ የሚገባው ፡ የመምህራን ፡ ኅብረትና ፡ የአስተያየት ፡ ተመሳሳይነትን ፡ ማግኘት ፡ ያስፈልጋል ። የትምህርት ፡ ዐይነቶችንና ፡ ሰዓቶችን ፡ አሟልቶ ፡ ለመወሰን ፡ የትምህርት ፡ አሰጣጥን ፡ ዘዴ ፡ ለማሻሻል ፡ በጥናትና ፡ በመመራመር ፡ ተግባር ፡ ሙሉ ፡ ኅብረትን ፡ ለማድረግ ፡ የሐሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሙንፈስ ፡ ፍላጎትና ፡ ቅንነት ፡ የተሟላ ፡ የሐሳብ ፡ መገናኛ ፡ ዘዴና ፡ መንገድ ፡ በጠቅላላው ፡ የጋራ ፡ ተግባርና ፡ ግዴታ ፡ ስሜት ፡ ጠልቆ ፡ ሲመሠረት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ድርጅት ፡ የተለያዩ ፡ አካሎችን ፡ ቢይዝም ፡ በመንፈስ ፡ የተዋሐደ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

በማናቸውም ፡ ግንኙነት ፡ በትምህርት ፡ አሰጣጥ ፡ ዘዴና ፡ በተማሪዎች ፡ አስተያየት ፡ ላይ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ የሚፈጥራቸው ፡ ብዙ ፡ ችግሮች ፡ አሉ ። የዩኒቨርሲቲ ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ ውጤት ፡ በትክክል ፡ ማሰብንና ፡ መመራመርን ፡ በማስቻል ፡ በሕግ ፡ መሣርያዎች ፡ እንዴት ፡ መጠቀምን ፡ እንደሚቻል ፡ መማር ፡ ነው ። የሕግ ፡ አዋቂ ፡ ሰው ፡ ተግባር ፡ ጠበቃም ፡ ሆነ ፡ ዳኛ ፡ ወይም ፡ አማካሪ ፡ ልዩ ፡ ዕውቀትን ፡ የሚጠይቅ ፡ ነው ። ይህም ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ በተለይ ፡ የጉዳዩን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ለይቶ ፡ ማወቅን ፡ የጉዳዩን ፡ የክርክር ፡ መሠረት ፡ አጣርቶ ፡ ማወቅን ፤ ሌሎች ፡ ጉዳዩን ፡ ለመረዳትና ፡ ለመፍታት ፡ የሚጠቅሙትን ፡ ግንኙነት ፡ ያሏቸውን ፡ ሁሉ ፡ ተመራምሮ ፡ ማወቅን ፡ የሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ደንቦችን ፡ በማወቅ ፡ ትክክለኛ ፡ ውሳኔን ፡ ለማስገኘት ፡ እንዴት ፡ እንደሚረዱ ፡ መረዳ

ትን ፥ እና ፥ በመጨረሻ ፥ ሐሳብን ፥ በትክክልና ፥ ውጤት ፥ ባለው ፥ መንገድ ፥ የመግለጽ ፥ ችሎታዎችን ፥ ጠቅሎ ፥ የያዘ ፥ ነው ። ደንበኛ ፥ የሕግ ፥ አዋቂ ፥ ሰው ፥ በቂ ፥ ዕውቀት ፥ በአእምሮው ፥ መያዝ ፥ ሲኖርበት ፥ (ይኸውም ፥ ማለት ፥ ስለተጻፉት ፥ ሕጎች) ፥ የዚህ ፥ ዐይነት ፥ ዕውቀት ፥ ከላይ ፥ በተዘረዘሩት ፥ ካልተደገፈ ፥ ግን ፥ ብቻውን ፥ አደገኛ ፥ ሊሆን ፥ ይችላል ። ስለዚህ ፥ የሕግ ፥ ትምህርት ፥ አሰጣጥ ፥ በፍጹም ፥ በቃል ፥ ጥናት ፥ ዘዴ ፥ ከሚሰጠው ፥ የተለየና ፥ ተቃራኒ ፥ መሆን ፥ አለበት ። ተማሪዎች ፥ በቃል ፥ ጥናት ፥ ሳይሆን ፥ በክፍልም ፥ ውስጥ ፥ ሆነ ፥ በውጭ ፥ ስለ ፥ ሕግ ፥ ጉዳይ ፥ መመራመርና ፥ መከራከርን ፥ መማር ፥ አለባቸው ።

ያነበቡትን ፥ ብቻ ፥ ደግሞ ፥ መናገር ፥ ከተማሪዎች ፥ የሚፈለግ ፥ ዕውቀት ፥ አለመሆኑን ፥ በብዙ ፥ ችግርም ፥ ቢሆን ፥ ማስተማር ፥ ዋና ፥ ግብ ፥ ነው ። ሊማሩ ፥ የሚገባው ፥ ሕግ፥ አንዳንድ ፥ ጊዜ ፥ ከላይ ፥ ሲመለከቱት ፥ ግልጽና ፥ ቀላል ፥ እየመሰለ ፥ ነገር ፥ ግን ፥ እውነተኛ ፥ ፍችው ፥ ጠልቆ ፥ በመመራመር ፥ ብቻ ፥ የሚገኝ ፥ መሆኑን ፥ ነው ። ሊማሩ ፥ የሚገባው ፥ ራሳቸውን ፥ እንዴት ፥ ማስተማር ፥ እንደሚችሉ ፥ ነው ። ሕጎች ፥ የማኅበራዊ ፥ ኑሮ ፥ ችግር ፥ መፍቻ ፥ መሣርያና ፥ የፖሊሲ ፥ መግለጫዎች ፥ መሆናቸውን ፥ መማር ፥ አለባቸው ። ሕግን ፥ በዚህ ፥ አስተያየት ፥ ማጥናት ፥ ይኖርባቸዋል ። በተለይም ፥ እዚህ ፥ አብዛኛው ፥ ሕግ ፥ አዲስ ፥ በሆነበት ፥ አገር ፥ ይህ ፥ በጣም ፥ አስቸጋሪ ፥ አቀራረብ ፥ ነው ።

ስለዚህ ፥ የሕግ ፥ ጥናት ፥ በጣም ፥ ጥንቃቄን ፥ የሚጠይቅ ፥ መመራመር ፥ በመሆኑ ፥ ለአዲስ ፥ የሕግ ፥ ተማሪዎች ፥ በጣም ፥ ተስፋ ፥ የሚያስቆርጥ ፥ ነው ። ምክንያቱም ፥ እያንዳንዱ ፥ ለማወቅ ፥ የሚጣጣር ፥ በመሆኑ ፥ ለማናቸውም ፥ ጥያቄ ፥ አንድ ፥ የተወሰነ ፥ ትክክል ፥ መልስ ፥ መኖር ፥ ስላለበት ፥ ይህ ፥ መልስ ፥ ሊነገረኝ ፥ ይገባል ፥ በማለት ፥ አስተያየት ፥ ስለሚመራ ፥ ነው ። ነገር ፥ ግን ፥ ብዙዎቹ ፥ የሕግ ፥ ጥያቄዎች ፥ የተወሰነ ፥ መልስ ፥ የላቸውም ። ስለዚህ ፥ በጣም ፥ ጠልቆ ፥ ማሰብንና ፥ ማጥናትን ፥ ይፈልጋሉ ። በእውነቱ ፥ ከሆነ ፥ መምህራን ፥ የማይሳሳቱ ፥ የሕግ ፥ አዋቂዎች ፥ አይደሉም ። እነሱም ፥ ቢሆኑ ፥ ይህን ፥ ካልተገነዘቡ ፥ አገልግሎት ፥ ሰጡ ፥ ሊባሉ ፥ አይቻልም ። ስለዚህ ፥ ብዙዎች ፥ ክፍል ፥ ውስጥ ፥ የሚቀርቡ ፥ ከባድ ፥ ጥያቄዎች ፥ ከክርክርና ፥ ሐሳብ ፥ መለዋወጥ ፥ በኋላ ፥ ምንም ፥ ውሳኔ ፥ ሳያገኙ ፥ ሐሳባቸው ፥ እንደተንጠለጠለ ፥ መታለፍ ፥ ይኖርባቸዋል ። ማናቸውም ፥ ተማሪ ፥ የሚያቀርበው ፥ ሐሳብ ፥ ሳይታረም ፥ ስለማይቀር ፥ በሙሉ ፥ ትክክል ፥ ሆኖ ፥ ተቀባይ ፥ የሚያገኝበት ፥ ጊዜ ፥ በጣም ፥ ያነሰ ፥ ነው ። በዚህ ፥ መንገድ ፥ ካልተረጋገጠ ፥ ውጤት ፥ ጋር ፥ መታገልና ፥ የ"ሶክራቲስ" ዐይነት ፥ ክርክር ፥ ብዙውን ፥ ጊዜ ፥ ተማሪዎችን ፥ በመጀመርያ ፥ ላይ ፥ ተስፋ ፥ ያስቆርጣል ። በተለይም ፥ የዚህ ፥ ዐይነት ፥ አቀራረብ ፥ በትምህርት ፥ አሰጣጥ ፥ ውስጥ ፥ ያልተለመደ ፥ በመሆኑ ፥ ከፍ ፥ ያለ ፥ ተስፋ ፥ መቍረጥን ፥ ያስከትላል ። ተማሪዎች ፥ የሕግ ፥ ድርሰት ፥ መጻፍም ፥ መማር ፥ ይኖርባቸዋል ። ይህም ፥ ጽሑፍ ፥ የሚታረመው ፥ ከፍ ፥ ካለ ፥ ነቀፌታ ፥ ጋር ፥ ነው ። ስለዚህ ፥ ብዙ ፥ ጊዜ ፥ ተደጋግሞ ፥ መጻፍ ፥ ይኖርበታል ። ተማሪዎች ፥ የራሳቸውን ፥ ሥራ ፥ ማረምና ፥ መንቀፍን ፥ መማር ፥ ይኖርባቸዋል ። ይህም ፥ በጣም ፥ ተስፋ ፥ የሚያስቆርጥ ፥ ነው ። ስለዚህ ፥ የመጀመርያው ፥ የሕግ ፥ ትምህርት ፥ ዓመት ፥ በጣም ፥ ከሁሉ ፥ የበለጠ ፥ ከባድ ፥ ነው ። በትምህርት ፥ ብቻ ፥ ሳይሆን ፥ በሳይኮሎጂም ፥ በኩል ፥ ብዙ ፥ መለማመድን ፥ ይጠይቃል ። እንዲሁም ፥ በየቀኑ ፥ እየተመራመሩና ፥ እየተማሩ ፥ በጣም ፥ በመሥራት ፥ ለሚሻሻሉት ፥ ወጣቶች ፥ ይህ ፥ ዓመት ፥ አዲስ ፥ አስተያየትና ፥ መንፈስ ፥ በመፍጠር ፥ የበለጠ ፥ ጠልቀው ፥ ወደ ፥ ፊት ፥ ለመመራመር ፥ የሚያስችላቸውን ፥ አስተያየት ፥ የሚፈጥሩበት ፥ ጊዜ ፥ ነው ። ሕግ ፥ አዋቂ ፥ ስለዚህ ፥ የሕግ ፥ ሥራ ፥ አባል ፥ የሚሆኑበት ፥ ዘመን ፥ ነው ።

መምህራንም ፥ እንዲህ ፥ ያለውን ፥ ችግር ፥ ለማቸነፍ ፥ በሚጣጣሩበት ፥ ጊዜ ፥ ብዙ ፥ ይማራሉ ። በአለፈው ፥ ዓመት ፥ የፈተና ፥ ወረቀቶችን ፥ ሌሎች ፥ የማስተማርያ ፥ ጽሑ

ፎችን ፣ የትምህርት ፡ ቤቱን ፣ ሪፖርቶች ፣ በማጥናት ፡ ስለ ፡ ትምህርቱ ፡ አሰጣጥ ፡ ዘዴና ፡ ደረጃ ፡ ለመገመት ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መጥተው ፡ ከነበሩት ፡ መርማሪዎች ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አትርፈናል ። ይህ ፡ የውጭ ፡ ገማቾችን ፡ ማምጣት ፡ የላቀ ፡ የአካዳሚ ፡ ደረጃ ፡ ለማግኛ ፡ ዋና ፡ መሠረት ፡ ስለሆነ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሳያቋርጥ ፡ የሚሠራበት ፡ ነው ። ሆኖም ፡ የመጀ መርያው ፡ ዓመት ፡ ሥራችን ፡ ውጤት ፡ የሚያኮራን ፡ ነው ።

## የሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ።

የሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ለሕግ ፡ ትምህርት ፡ እምብርቱ ፡ ነው ። ለአንድ ፡ የሕግ ፡ አዋቂ ፡ መጻሕፍት ፡ ዋና ፡ መሣሪያው ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ በሕግ ፡ ሞያ ፡ የምንተዳ ደር ፡ ሁሉ ፡ በመጻሕፍትና ፡ ከነሱ ፡ በምናገኘው ፡ ሐሳብ ፡ መገልገል ፡ ይኖርብናል ። የሕግ ፡ ምንጮች ፡ የሆኑትን ፡ የተውጣጡ ፡ ሕጎች ፡ ደንቦችና ፡ ድንጋጌዎች ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ዎችና ፡ የሕግ ፡ ተመራማሪዎች ፡ የደረሷቸውን ፡ ጽሑፎች ፡ ተማሪው ፡ ለማግኘት ፡ የሚ ችለው ፡ ከቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ነው ። የሕግ ፡ ተማሪ ፡ ትምህርቱ ፡ ተፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ለወደፊትም ፡ በሕግ ፡ ሞያው ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ የዕለት ፡ ተግባሩ ፡ ሆኖ ፡ የሚያገኘ ውን ፡ የግል ፡ ጥናትና ፡ ከፍተኛ ፡ መመራመር ፡ ሊያደርግ ፡ የሚችለው ፡ በቤተ ፡ መጻሕ ፍት ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ከፎርድ ፡ ፋውንዴሽን ፡ በተገኘ ፡ ስጦታ ፡ ተረድቶ ፡ ለሕግ ፡ ትም ህርት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለሕግ ፡ ሞያተኞች ፡ ጠቃሚ ፡ አገልግሎት ፡ የሚሰጥ ፡ የሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ አቋቁሟል ። በ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መጻሕፍት ፡ ቤቱ ፡ ፫ሺ ፡ መጻሕፍት ፡ ከነሙሉ ፡ ድርጅቱ ፡ ነበሩት ። በልግስናቸው ፡ የምንፈልጋቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ እንድናገኝ ፡ ስጦታ ፡ ላደረጉልን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ ዩኒቨር ሲቲዎችና ፡ እንዲሁም ፡ የግል ፡ ለጋሶች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋናችንን ፡ ሳንገልጽ ፡ አናል ፍም ። ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ በመጻሕፍቱ ፡ አያያዝ ፡ ልዩ ፡ ሞያ ፡ ያለው ፡ ቋሚ ፡ ሠራተኛ ፡ ሲኖረው ፡ እንዲሁም ፡ ተማሪዎች ፡ በረዳትነት ፡ ያገለግላሉ ። ስለ ፡ ሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ልዩ ፡ ሞያ ፡ ያለው ፡ አማካሪ ፡ የሚያስፈልጉንን ፡ መጻሕፍቱ ፡ አግኝተን ፡ እንድንገዛ ፡ በአ ማካሪነት ፡ ያገለግለናል ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣዎች ፡ በሙሉ ፡ እንዲሁም ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ሌሎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግጋትና ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የተጻፉ ፡ ጥራዞች ፡ ጽሑፎች ፡ አሉት ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ አፍሪካ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ኮመን ፡ ሎው ፡ ስለ ፡ ሮማውያን ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሲቪል ፡ ሎው ፡ እንተርናሽናል ፡ ሕግና ፡ ስለ ፡ ኮምፓራቲቭ ፡ ሎው ፡ የተለዩ ፡ ክፍሎች ፡ አሉት ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ የትምህርት ፡ መስጫ ፡ መጻሕፍት ፡ እንዲሁም ፡ "ትሪታይሲስ" ፡ የሕግ ፡ መጽሔቶች ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ዎችና ፡ በሕግ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሶሺያል ፡ ሳይንስ ፡ ጭምር ፡ ምርጥ ፡ የሆኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጽሑፎች ፡ ይገኙበታል ።

## የከብር ፡ ዝግጅት ፡ (ቅንጅት) ።

ራስን ፡ በራስ ፡ ማስተዳደር ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤታችን ፡ የሚገቡ ፡ ተማሪዎች ፡ ልዩ ፡ ሞያ ፡ ለማግኘት ፡ የሚሹ ፡ ናቸው ። በዚህም ፡ ሞያ ፡ ሐቀኝነት ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ተሰጥቶት ፡ የሚሠራበት ፡ መሆኑን ፡ በመረዳት ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ተማ ሪዎች ፡ በገዛ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ራስን ፡ በራስ ፡ ለመግዛትና ፡ እውነተኛ ፡ በመሆን ፡ ራሳቸ ውን ፡ ለማመንና ፡ እንዲሁም ፡ ከፋኩልቲው ፡ ጋር ፡ በሚያደርጉት ፡ ግንኙነት ፡ ሁሉ ፡

ተግባራቸው ፡ እውነተኛ ፡ ትክክለኛና ፡ ሐቀኛ ፡ ሆኖ ፡ ሙሉ ፡ እምነት ፡ ተጥሎባቸው ፡ አንዳች ፡ መቆጣጠር ፡ ሳያስፈልጋቸው ፡ ራስን ፡ በራስ ፡ የመግዛት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብተዋል ። በፈተናም ፡ ጊዜ ፡ በዚሁ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ መሠረት ፡ ተማሪዎች ፡ መምህሩ ፡ ባልፈቀደው ፡ እርዳታ ፡ ሳይጠቀሙ ፡ ያለአንዳች ፡ መቆጣጠር ፡ እምነት ፡ ተጥሎባቸው ፡ ይሠራሉ ። ራስን ፡ በራስ ፡ የመግዛት ፡ ደንብ ፡ ለማውጣትና ፡ ለማስተዳደር ፡ ኀላፊነት ፡ ተሰጥቶት ፡ በተማሪዎች ፡ ተመርጦ ፡ የተቋቋመ ፡ አንድ ፡ ቦርድ ፡ አለ ። የቦርዱ ፡ ተግባር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ስለማፍረስ ፡ የቀረቡለትን ፡ ክስ ፡ በማጥናት ፡ በአጥፊው ፡ ላይ ፡ ተገቢው ፡ እርምጃ ፡ እንዲወሰድ ፡ ለዲኑ ፡ አስተያየት ፡ ማቅረብ ፡ ነው ።

## <u>የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር</u> ።

የሕግ ፡ ሞያ ፡ እጩ ፡ አባሎች ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ተማሪዎች ፡ ራሳቸውን ፡ የሚያስተዳድሩበት ፡ አንድ ፡ አቋም ፡ አላቸው ። በተማሪዎች ፡ የተመረጡ ፡ እንደራሴዎች ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ለመወያየት ፡ ከፋኩልቲው ፡ አባሎች ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ያደርጋሉ ። ማኅበሩ ፡ ራስን ፡ በራስ ፡ ስለማስተዳደር ፡ በመጻሕፍት ፡ ቤት ፡ መጠቀም ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ስለ ፡ ፈተና ፡ አቀባበልና ፡ ስለሌሎችም ፡ ጉዳዮች ፡ ደንብ ፡ አውጥቶአል ። የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ በዓመቱ ፡ ውስጥ ፡ ጠቃሚ ፡ ትርኢቶች ፡ አዘጋጅቶ ፡ ከማቅረቡም ፡ በላይ ፡ በየዓመቱ ፡ የሕግ ፡ ቀን ፡ ተብሎ ፡ የሚከበርና ፡ በሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ፊት ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ የመከራከር ፡ ችሎታቸውን ፡ ለማሳየት ፡ ውድድር ፡ ካደረጉት ፡ ተማሪዎች ፡ ውስጥ ፡ ብልጫ ፡ ያገኙት ፡ የመጨረሻ ፡ ክርክር ፡ የሚያደርጉበትን ፡ ዕለት ፡ ያዘጋጃል ። የሕግ ፡ ተማሪዎቻችን ፡ ብዛት ፡ እያደገ ፡ በሄደ ፡ ቍጥር ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ ስለሚያጋጥሙት ፡ ችግሮችና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ እድገት ፡ አጥብቆ ፡ የሚከታተል ፡ ልዩ ፡ ሙያ ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ አቋም ፡ እንደሚሆን ፡ ተስፋ ፡ ይደረጋል ።

## <u>የትምህርት ፡ አሰጣጥ ፡ ፕሮግራም</u> ።

ሀ) <u>የሦስት ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ ዲግሪ ፡ ፕሮግራም</u> ፤ ይህን ፡ ፕሮግራም ፡ የሚከታተሉ ፡ ፭፩ ፡ የቀን ፡ ተማሪዎች ፡ ተቀብለናል ። ይህን ፡ ፕሮግራም ፡ ለመከታተል ፡ ተማሪው ፡ ቢያንስ ፡ ሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ መጨረስና ፡ በቂ ፡ ትምህርትና ፡ ከፍተኛ ፡ ውጤት ፡ እንዲኖረው ፡ ይፈለግበታል ። አሁን ፡ ከተቀበልናቸው ፡ ተማሪዎች ፡ ይበልጡዎቹ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ትምህርት ፡ ያላቸው ፡ ሲሆኑ ፡ ብዙዎቹ ፡ ደግሞ ፡ የሥራ ፡ ልምድ ፡ ጭምር ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ። የሕግ ፡ ድግሪ ፡ ለማግኘት ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ መማር ፡ ያስፈልጋል ።

ለ) <u>የአራት ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ ዲግሪ ፡ ፕሮግራም</u> ፤ ለአራት ፡ ዓመት ፡ በማታ ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጥ ፡ የሕግ ፡ ዲግሪ ፡ የሚከታተሉ ፡ ፵ ፡ ተማሪዎች ፡ ተቀብለን ፡ ነበር ። የዚህም ፡ ፕሮግራም ፡ ዓላማ ፡ የሕግ ፡ ዲግሪ ፡ ለመከታተል ፡ በቂ ፡ ችሎታ ፡ ኖሯቸው ፡ ኀላፊነት ፡ ባለው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በመሆናቸው ፡ ሥራቸውን ፡ ትተው ፡ በቀን ፡ ተማሪነት ፡ ሊከታተሉ ፡ ለማይችሉት ፡ ሰዎች ፡ ዕድል ፡ ለመስጠት ፡ ሲሆን ፡ በመሠረቱ ፡ የማታው ፡ ፕሮግራም ፡ ከቀኑ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ። አንድ ፡ ዐይነት ፡ ትምህርትና ፡ ፈተና ፡ ተሰጥ

ቷቸው ፡ የፈተናው ፡ ወረቀታቸው ፡ ስም ፡ ሳይጻፍበት ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ተማሪ ፡ በተሰ ጠው ፡ ቊጥር ፡ ብቻ ፡ ተለይቶ ፡ በምስጢር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ይታረማል ።

የማታው ፡ ትምህርት ፡ ከፍተኛ ፡ ጥረት ፡ ይጠይቃል ። እስካሁንም ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ልፋት ፡ ያጋጠመ ፡ ሲሆን ፡ ለወደፊትም ፡ እንደዚሁ ፡ ይቀጥላል ። ሆኖም ፡ ጥረታቸውን ፡ በመቀጠል ፡ ኮርሱን ፡ የሚከታተሉት ፡ ለራሳቸው ፡ የግል ፡ ጥቅም ፡ ከማትረፋቸውም ፡ በላይ ፡ የሕግ ፡ ሞያ ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንዲስፋፉ ፡ እንደሚረዱ ፡ ተስፋ ፡ ይደረጋል ።

ሐ) <u>የሕግ ፡ የምስክር ፡ ወረቀትና ፡ የዲፕሎማ ፡ ፕሮግራም</u> ፤ በሕግ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ትምህርት ፡ ያላቸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በአማርኛ ፡ የሚሰጥ ፡ የሕግ ፡ ኤክስቴንሽን ፡ ትምህርት ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ጀምረው ፡ ፕሮግራሙ ፡ የሕግ ፡ ፋኩሊቲ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ሆኗል ። ትምህርቱ ፡ በትርፍ ፡ ጊዜ ፡ ለሁለት ፡ ዓመት ፡ ተመ ንፈቅ ፡ የሚሰጥ ፡ ሲሆን ፡ በሚገባ ፡ ተከታትለው ፡ ለጨረሱት ፡ የሕግ ፡ ምስክር ፡ ወረ ቀት ፡ ይሰጣል ። የትምህርቱ ፡ ፕሮግራም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ የያዘ ፡ ነው ። ትምህር ቱን ፡ ለመከታተል ፡ የአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ በሚገባ ፡ ማወቅና ፡ ደግሞም ፡ ከሕግ ፡ ኤክስቴ ንሽን ፡ ፕሮግራም ፡ ለመጠቀም ፡ የሚችሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ለተቋቋመ ፡ ኮሚቴ ፡ ማረጋገጥ ፡ ያስፈልጋል ።

የመጀመሪያዎቹ ፡ ፳፪ ፡ ተማሪዎች ፡ በሰኔ ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኮርሱን ፡ የጨረሱ ፡ ሲሆን ፡ ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ዳኞች ፡ ጠበቆችና ፡ ሌሎች ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ይገኙበታል ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በተገኙበት ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ የተደረገው ፡ ሽልማት ፡ ምረቃ ፡ ክብረ ፡ በዓል ፡ በመዘከር ፡ ላይ ፡ ተቀርፆ ፡ የሚቀርና ፡ ልብን ፡ የሚነካ ፡ ነው ።

በመጀመሪያው ፡ ዓመታችን ፡ ውስጥ ፡ የማታ ፡ የሕግ ፡ ዲፕሎማ ፡ ፕሮግራም ፡ በ መጨመር ፡ የትርፍ ፡ ሰዓት ፡ የሕግ ፡ ትምሕርትን ፡ ለማስፋፋት ፡ ወሰን ። የዚህ ፡ ፕሮ ግራም ፡ የማስተማሪያ ፡ ቋንቋም ፡ እንግሊዝኛ ፡ ነው ። የመግቢያ ፡ ፈተናው ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ ሲኾን ፡ ትምህርቱ ፡ ጥልቅና ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ዓመት ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ለዚሁ ፡ ፕሮግራም ፡ ዘጠና ፡ የሚኾኑ ፡ ተማሪዎች ፡ ተቀበልን ።

እንደዚሁም ፡ በዚህ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመታችን ፡ ውስጥ ፡ ይህንኑ ፡ የመሰለ ፡ የኤክስቴንሺን ፡ ፕሮግራም ፡ አሥመራ ፡ ላይ ፡ የሚቋቋምበትን ፡ መንገድ ፡ በየጊዜው ፡ ስንነጋገርበትና ፡ ስንወያይበት ፡ እንደነበረም ፡ መግለጹ ፡ ይገባኛል ። በዚሁ ፡ ዓመት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡ የሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ትምህርቶች ፡ በአሥመራ ፡ ውስጥ ፡ አቋቊመናል ። እነዚህም ፡ ትምህርቶች ፡ ደንበኛ ፡ የኤክስቴንሺን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መጀመሩን ፡ የሚያበሥሩና ፡ ተስፋ ፡ የሚጣልባቸው ፡ ናቸው ።

## <u>የሕግ ፡ መጽሔትና ፡ ምርመራ ።</u>

ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የተጻፉ ፡ ጉዳዮች ፡ በብዛት ፡ ስለሌሉ ፡ ለማግኘት ፡ አስቸ ጋሪ ፡ ነው ። ስለ ፡ ሕግ ፡ የወጡት ፡ የመሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ማብራሪያዎች ፡ ካልተገኙ ፡ አንድን ፡ ሕግ ፡ ለመረዳትና ፡ በሚገባ ፡ በሥራ ፡ ለማዋል ፡ አይቻልም ። የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ከብዙ ፡ ምንጭ ፡ የተውጣጣ ፡ በመሆኑ ፡ ሕጉን ፡ ለመረዳት ፡ ከምንጩ ፡ አንስቶ ፡ ማጥናት ፡ ያስፈልጋል ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የተደረገ ፡ ጥናት ፡ እነስ

ተኛ ፡ ነው ። እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ስለወጡት ፡ ሕጎች ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ የሚያስረዱ ፡ ማብራሪያዎች ፡ የሉንም ። ታትመው ፡ የወጡ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውሳኔ ፡ አዘጋጅተው ፡ የሚሰጡ ፡ ሪፖርቶች ፡ የሉም ። ሕግን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለሚያውሉት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሚያገለግል ፡ መሠረታዊ ፡ መምሪያ ፡ የለም ። በየቀኑ ፡ የሚያጋጥሙትን ፡ አያሌ ፡ የሆኑ ፡ ጥልቅ ፡ የሕግ ፡ ፕሮብሌሞች ፡ ለምሳሌ ፡ በአደጋ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚነሱ ፡ የካሳ ፡ ጥያቄ ፡ አወሳሰን ፡ በቀረጥ ፡ የወጡትን ፡ ሕጎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለማዋል ፡ በመሬት ፡ ይዞታና ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ረገድ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ድርጊቶች ፡ ስለከተማ ፡ መስፋፋት ፡ ስለውጭ ፡ አገር ፡ እንቬስትሜንት ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ ስለማዳበር ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለማዋል ፡ ስለአስተዳደር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተወሰደ ፡ ጥናት ፡ የለም ። አዲስ ፡ በወጡት ፡ ሕጎች ፡ በመጠቀም ፡ ረገድ ፡ የሚያጋጥሙትን ፡ ችግሮች ፡ ለመረዳት ፡ የሚጠቅሙ ፡ ቀድሞውን ፡ ስለመሬት ፡ ይዞታና ፡ ስለሌሎች ፡ የሕግ ፡ አቋሞች ፡ ማወቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ታትሞ ፡ የወጣ ፡ መረጃ ፡ አነስተኛ ፡ ነው ።

ለሀገር ፡ ጠቃሚ ፡ ሆኖ ፡ ለመገኘት ፡ ተሻሽሎ ፡ የወጣውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥትና ፡ የጥንቱን ፡ የአገር ፡ ልማድ ፡ አጠናቅቀው ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ። ስለዚህ ፡ የፋኩልቲ ፡ አባሎች ፡ እንዲሁም ፡ ሌሎችም ፡ ተመራማሪዎችና ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ የትምህርት ፡ መስጫ ፡ መጻሕፍቶችን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ሌሎች ፡ ጽሑፎችንም ፡ አዘጋጅተዋል ። ይህም ፡ እንደ ፡ መጀመሪያ ፡ እርምጃ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጥናትና ፡ ምርመራ ፡ እንስቲቱት ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ ስለ ፡ መሬት ፡ ይዞታ ፡ ሁለት ፡ የምርመራ ፡ ውጤት ፡ በሚቀጥለው ፡ መጽሔት ፡ እንዲወጡ ፡ ለእትም ፡ ተሰጥተዋል ። ሌሎች ፡ ምርመራዎች ፡ በመቀጠል ፡ ላይ ፡ ስለሆኑ ፡ ተፈጽመው ፡ ውጤት ፡ ሲሰጡ ፡ ላስታውቃችሁ ፡ እጠባበቃለሁ ።